## ተፈጸመ ትስብእት፡ በኢትዮጵያ ማርያም ድንግል!
## በብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል፡ ዜናዌ ቃል!

ይድረስ፡ ለኪዳናውያት እና ለኪዳናውያን፡ "የእግዚአብሔር እና የኢትዮጵያ ልጆች"፥ እኅቶቼና ወንድሞቼ፥ የክህነት ባልደረቦቼም!

በሰማያቱ የዘለዓለም አባታችንና እናታችን ስም፡ ከነቤተሰባችሁ፡ በያላችሁበት፡ "እንዴት አላችሁ!" እያልሁ፡ ኪዳናዊና ኢትዮጵያዊ ሰላምታዬን፡ አቀርብላችኋለሁ። ለእነርሱ፡ ምስጋናችን ይድረሳቸውና፡ ዐብረውኝ ካሉት ጋር፡ እኔ ደኅና ነኝ።

ይህን ደብዳቤ እንድጽፍላችሁ መነሻ የኾነኝ ምክንያት፡ እንደተለመደው፡ ወደፊት፡ በመካከላችን፡ የደብዳቤ ልውውጥ በምናደርግበት ጊዜ፡ በዚህ ረገድ ያለውን የጽሕፈት አያያዛችንን አካኼድና የአሠራራችንን አፈጻጸም ለማቅለልና ለማቀላጠፍ ይቻለን ዘንድ፡ ልንከተለው ስለሚገባን ሥርዓት፡ አሳብ ላቀርብላችሁ ስለፈለግሁ ነው።

### መጀመሪያ

በማቀርብላችሁ፡ በዚህ አሳብ መሠረት፡ በየደብዳቤያችን ላይ፦

፩. **"እግዚአብሔር"** ስንል፡ እግዚአብሔር አብን እና እግዚአብሔር እምን፡ እርሷም፡ ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ ድንግል ማርያምን፥ እንዲሁም፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሢሕን እና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስንም አካትተን መጥራታችን ነው።

፪. **"ማርያም"** ስንል፡ **"እመ-አርያም"**፡ ማለታችን ነው።

**"ማርያም"** የሚለው ስም፡ ጥንተ ትርጓሜው፡ ይህ ነውና። **"አርያም"**፡ "ፍጹም፥ ምሉእ፡ ሰማያተ፥ ወምድረ!"

ማለትም፡ "በሰማያትና በምድር በተጠቃለለው፡ በፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ ፈጽሞ የሞላው፥ 'ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ!' ተብሎም የሚመሰገነው እግዚአብሔር የሚኖርበት" ማለት ሲኾን፡ **"እመ-አርያም"**፥ ወይም፡ **"ማርያም"**፡ የዚያ መለኮታዊ ህልውና መኖሪያ፡ **"እናት"**፥ ወይም፡ **"እመቤት"**፥ ወይም፡ **"ባልተቤት"** ማለት ነው።

፫. **"ቅድስት ሥላሴ"** ስንል፡ "አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ፡ ሦስቱም፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ እግዚአብሔር የኾኑባት፡ እርሷ፡ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም መኾኗን መናገራችን ነው።

፬. እየራሳችንን፡ "ኪዳናዊ" እና/ወይም፡ "ኪዳናዊት" ስንል፡ ለዚህ ጸጋና ክብር የበቃነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ በፍጹም በማመናችንና በዚሁ እምነት፡ የቃል ኪዳን ምስክርነትን በመስጠታችን፥ በአንገታችንም ላይ፡ የኖኅ ቃል ኪዳን ምልክት የኾነውንና የቀስተ ደመና አረንጓዴ፥ ብጫ፥ ቀይ ቀለማትን የያዘውን ማተብ ማጥለቃችንን፥ ከዚህ የተነሣ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዚአብሔር እም ኢትዮጵያ ልጆችና ዜጎች፥ ካህኖችና ነጋሢዎች የመኾንን ጸጋና ክብር በመቀዳጀታችን መኾኑን፡ ለእየራሳችንና ለእርስ በርሳችን ማረጋገጣችን ነው።

፭. ስለዚህ፡ "ለኪዳናዊት እከሊት!" እና/ወይም፡ "ለኪዳናዊ እከሌ!" ብለን፡ ሥጋዊዉን/ምድራዊዉን (የዓለም)፥ ወይም፡ መንፈሳዊዉን/ሰማያዊዉን (የጥምቀት) ስማችንን፡ ከኹለት፤ አንዱን ብቻ፡ ጠቅሰን ስንጽፍ፡ "በቅዱሱ ኪዳን፡ ለተወደድሽና ለተከበርሽ ኪዳናዊት እኅቴ፥ ክህነታዊት ባልደረባዬም!" እና/ወይም፡ "ለተወደድህና ለተከበርህ ኪዳናዊ ወንድሜ፥ ክህነታዊ ባልደረባዬም!" ማለታችን መኾኑን እናውቃለን።

፮. ሥጋዊው/ምድራዊው (የዓለም)፥ እና፡ መንፈሳዊው/ሰማያዊው (የጥምቀት) ስማችን፡ ኹለቱም፡ "ስምን መልአክ ያወጣዋል!" በሚለው ሃይማኖታዊ ይትበሃላችን መሠረት፡ የተቀደሱ ስሞቻችን ስለኾኑ፡ እንዳስፈላጊነቱና እንደየአግባቡ፡ ከኹለቱ፡ በአንደኛው፡ በማንኛውም ስማችን ስንጠራራና ስንጻጻፍ፡ ይህ አጠራራችንና አጻጻፋችን፡ ምንም ልዩነት እንደሌለው እንገነዘባለን።

፯. ይህን ሥርዓት፡ በዚህ መልክና ይዘት ስንፈጽመው፡ እያንዳንዳችን ኪዳናውያትና ኪዳናውያን፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጅነታችን፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያም ዜግነታችን፥ ነጋሢነታችንና ካህንነታችን፥ እኅትነታችንና እኅትማማችነታችን፥ ወንድምነታችንና ወንድማማችነታችን፥ መወደዳችንና መዋደዳችን፥ መከበራችንና መከባበራችን፡ በእርስ በርሳችንና በመካከላችን ዘንድ ብቻ ተወስኖ የሚገታና የሚቀር ሳይኾን፥ በይበልጥ፡ በሰማዩ አባታችንና በሰማይዋ እናታችን፥ በሰማያቱ ጉባኤም ዘንድ፡ ቋሚ ተቀባይነትንና ተፈጻሚነትን አግኝቶ፡ በታላቅ ሓሤት የሚገለጽ መኾኑ፥ እኛም፡ በየግላችን፡ በኹለቱም ስሞቻችን፡ በእግዚአብሔር የሕይወት መጽሓፍ ውስጥ የተመዘገብን መኾናችን መረጋገጡን እናጸናለን።

## ኹለተኛ

"ቅድስት ሥላሴ" የኾነችው፡ የቅድስት ድንግል ማርያም፡ ስምና ዝክረ ነገር፡ እዚህ ላይ ከተነሣ ዘንድ፡ ከዚህ ጋር የተያያዙ፡ አንዳንድ፡ የተለመዱና የቅርብ እውነቶችን፡ እስኪ ላክልላችሁ!

፩. ከላይ፡ በመጀመሪያው ርእስ፡ «"ቅድስት ሥላሴ" ስንል፡ "አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ፡ ሦስቱም፡ በተዋሕዶ ምሥጢር፡ አንድ እግዚአብሔር የኾኑባት፡ እርሷ፡ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ ድንግል ማርያም መኾኗን መናገራችን ነው።» የሚለውን አማናዊ ቃል፡ ለማረጋገጥ፡ ከዚህ የሚከተለውን ሰማያዊ መልእክት በማስተዋል መመልከቱ ተገቢ ይኾናል፦

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ በእግዚአብሔር እናትነቷ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በሰውነት የወለደችበትን ፅንሰቷን ባበሠረባት፡ በምሥራቹ ቃል፡ "**መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ!**"

ማለትም፡ "**መንፈስ ቅዱስ፡ በአንቺ ያድራል!**" ባላት ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ከእርሷ ጋር በተዋሕዶ መኖሩን፥

"**ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ!**"

ማለትም፡ "**የልዑል ኃይል ይጸልልሻል (ያቅፍሻል)!**" ባላት ጊዜ፡ እግዚአብሔር አብ፡ ከእርሷ ጋር በተዋሕዶ መኖሩን፥

"**ዝኒ ይትወለድ እምኔኪ፡ ቅዱስ ውእቱ፡ ወይሰመይ፡ 'ወልደ እግዚአብሔር ልዑል!'**"

ማለትም፡ "**ከአንቺ የሚወለደው እርሱ፡ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ፡ ቅዱሱ እግዚአብሔር ነው!**" ባላት ጊዜ፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ከእርሷ ጋር በተዋሕዶ መኖሩን መስክሮአል።

በዚህም እውነታ፡ "ድንግል ማርያም፡ ከፍጥረተ ዓለሙ አስቀድሞ፡ በቅድስት ሥላሴነቷ፡ የሦስቱም አንድነት መገኛ እንደነበረች ኹሉ፡ ከፍጥረተ ዓለሙም በኋላ፡ በዘመነ ሥጋዌ፡ እንዲሁ፡ በቅድስት ሥላሴነቷ፡ የሦስቱም መገኛ መኾኗ፡ ተረጋግጦ ታወቀ፤ ተረዳ!" ማለት ነው።

፪. ለእነርሱ የምናቀርበውን ስባሔያችንንና ውዳሴያችንን፥ ቅዳሴያችንንና ማኅሌታችንን፥ ሰዓታታችንንና ምሕላችንን ጨምሮ፡ የማንኛውም ዓይነት፡ የግልና የማኅበር ሥርዓተ ጸሎታችን መክፈቻ፡ ምን እንደሚል ታውቃላችሁ፤

እርሱም፦ "አአትብ ገጽየ፥ ወኵለንታየ፡ በትእምርተ መስቀል!"

ማለትም፡ "ፊቴንና ኹለንተናዬን፡ በመስቀል ምልክት አማትባለሁ!" እያልን ካማተብንና ከሰገድን በኋላ፡

"በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፥ እንዘ አአምን፥ ወእትመሓፀን፤ እክሕደከ ሰይጣን፡ በቅድመ ዛቲ፡ እምየ ቅድስት ኢትዮጵያ መንግሥተ እግዚአብሔር፣ እንተ ይእቲ፡ ስምዕየ ማርያም ጽዮን፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።"

ማለትም፡ "'አብ፥ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ' በሚሉ፡ የሦስትነት ስሞች ታውቆ፡ በአንድነት የነጠላ ስም የሚጠራውን፡ እግዚአብሔርን፡ አንድ አምላክ ባደረገችው፥ ቅድስት ሥላሴ እና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው፡ በእናቴና በምስክሬ፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ጽዮን (መጠጊያዬ)፡ አምኜና ተማጽኜ፡ በእርሷ ፊት፡ አንተን፡ ሰይጣንን ክጄሃለሁ፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።" ብለን የምናሰማው ጸሎት ነው።

፫. የሌሊት፥ የነግህና የሠርክ ኪዳናዊ ጸሎታችን መግቢያ፡ እንዲህ የሚል መኾኑንም ታውቃላችሁ፡- "ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፡ ዘኢይመውት! ዘተወልደ፡ እማርያም፥ እምቅድስት ድንግል፤ ተሣሃልከነ እግዚኦ!"

ማለትም፡ "በቅድስት ሥላሴነቷ አንድ ካደረገችው፡ ከማይሞተውና ቅዱስ ከኾነው ከእግዚአብሔር አብ፥ ደግሞም፡ ሕያውና ቅዱስ ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር፡ አንዱ ቅዱስ የኾነው እግዚአብሔር ወልድ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፡ ስርየትን አስገኘልን!"

"ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፡ ዘኢይመውት! ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ፤ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል፤ ተሣሃልከነ እግዚኦ!"

ማለትም፡ "በቅድስት ሥላሴነቷ አንድ ካደረገችው፡ ከማይሞተውና ቅዱስ ከኾነው ከእግዚአብሔር አብ፥ ደግሞም፡ ሕያውና ቅዱስ ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር፡ አንዱ ቅዱስ የኾነው እግዚአብሔር ወልድ፡ በዮርዳኖስ ተጠምቆ፥ በመስቀልም ላይ ተሰቅሎ፡ ይቅርታን አስገኘልን!"

"ቅዱስ እግዚአብሔር፥ ቅዱስ ኃያል፥ ቅዱስ ሕያው፡ ዘኢይመውት! ዘተንሥአ እሙታን፡ አመ ሣልስት ዕለት፤ ዐርገ በስብሓት ውስተ ሰማያት፤ ወነበረ በየማነ አቡሁ፤ ዳግመ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኴንን ሕያዋነ፥ ወሙታነ፤ ተሣሃልከነ እግዚኦ!"

ማለትም፡ "በቅድስት ሥላሴነቷ አንድ ካደረገችው፡ ከማይሞተውና ቅዱስ ከኾነው ከእግዚአብሔር አብ፥ ደግሞም፡ ሕያውና ቅዱስ ከኾነው፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር፡ አንዱ ቅዱስ የኾነው እግዚአብሔር ወልድ፡ በሦስተኛው ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፤ በክብር፡ በምስጋና፡ ወደሰማያት ዐረገ፤ በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ፡ በገናናነት ይመለሳል፤ እንዲህ አድርጎ፡ ምሕረትን አስገኘልን!"

እንግዴህ፡ እውነታው፡ ይህ ከኾነ፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በፅንሰቱና በልደቱ ጊዜ ብቻ ሳይኾን፡ በጥምቀቱና በስቅለቱ፥ በሞቱና በትንሣኤውም ጊዜ፡ እግዚአብሔር አብና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡ እንዳልተለዩት ኹሉ፡ በመለኮቱና በሰውነቱ፡ እናቱ ኾና፡ ወልዳ ያሳደገችው፡ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያምም፡ በቅድስት ሥላሴነቷ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ብቻ ሳይኾን፡ በመለኮታዊው አካልና ባሕርይ ጭምር፡ በእነዚህ ኹሉ ጊዜያት፡ ዐብራው እንደነበረችና ምንጊዜም እንዳልተለየችው፡ "እሙን ኾነ!" ማለት ነው።

በቅድስት ሥላሴ ሰላምና ፍቅር፥ ጸጋና በረከት፡ በያለንበት ስለምንኖር፡ ደስ ይበለን!

ጥር ፫ ቀን፥ ፳፻፯ ዓመተ ምሕረት።

በቅዱሱ ኪዳን፡ አክባሪ ወንድማችሁና የአገልግሎት ባልደረባችሁ፡-
ንቡረ-እድ ኤርምያስ/ኂሩተ ወልድ።